በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

# ተመዘኑ!

/በአንድ አካባቢ ሚዛን ይዞ ተመዘኑ እያለ ሚጣራ አንድ መዘኛ ነበር።/

<u>መዛኝ፡</u> ተመዘኑ ተመዘኑ .. በአባቶቻችሁ ሚዛን ተመዘኑ ፣ ተመዘኑ ፣ ራቁታችሁን ተመዘኑ .. ራቁታችሁን ተመዘኑ

<u>መንገደኛ፡</u> ምን የቀባጥራል? ራቁታችሁን ተመዘኑ?

<u>መዛኝ፡</u> ና ወንድሜ በሚሰጥራዊው ሚዛን ተመዘን

<u>መንገደኛ፡</u> ባክህ ለቀልድ ግዜ የለኝም /እልፎ ይሔዳል/

<u>መዛኝ፡</u> ለምን ግን ራቁታችንን መሆን እንፈራለን? በእግዚአብሔር ፊት እኮ ሁልግዜ ራቁታችንን ነን! ደግሞ ለቀልድ ግዜ የለኝም ይላል? ይሄኔ እኮ ኮሜዲ ፊልም ለማየት ሲኒማ ቤት ሊሰለፍ ይሆናል ሚሄደው .. ለቅደሴ ግዜ የለኝም፤ ለጸሎት ግዜ የለኝም . ለመመዘንም ግዜ የለኝም፣ ለሰንፍና ግን (የመገረምም የመበሳጨትም ስሜቱን በእጁ እያሳየ) ..... ተመዘኑ ፣ ተመዘኑ በምስጢራዊው ሚዛን ራቁታችሁን ተመዘኑ .

<u>ዳዊት፡</u> ምን አይነት ሚዛን ነው እንዲህ ሚሞካሸው?

<u>መዛኝ፡</u> በጣም ጥሩ ሚዛን ነው።

/ዳዊት ሚዛን ላይ ሊወጣ ሲል/ ቆይ ቆይ! ከዚያ በፊት ጥቂት የምጠይቅህ ጥያቄዎች አሉኝ

ዳዊት፡ እንዴ አንተ ራስህ ነህ እንዴ ሚዛኑ . እሺ ቀጥል ጥያቄህን

መዛኝ፡ ስምህ ማነው?

ዳዊት፡ ዳዊት፣ አንዳንዶች ጎልያድ ይሉኛል።

መዛኝ፡ በቀን ስንት ግዜ ትበላለህ?

ዳዊት፡ ያምሃል እንዴ? አሁን ይሄ ምን ያደርግልሃል? ለማንኛውም በቀን 4 ግዜ ብቻ እበላለሁ፣ ቁርስ፣ ምሳ፣ መክሰስ፣ ራት። ሌላ ጥያቄ አለህ?

መዛኝ፡ በአንድ የምግብ ግዜ ስንት ደቂቃ ትጠቀማለህ?

ዳዊት፡ እኔ እንጃ፣ ሳይህ ገማች ትመስላለህ፤ በግምት ፃፈው

መዛኝ፡ 20 ደቂቃ?

ዳዊት፡ አላልኩህም አሪፍ ገማች ነህ

መዛኝ፡ ይሄ ማለት በ4 የምግብ ግዜ በድምሩ በቀን 80 ደቂቃ ወይም 1ሰዓት ከ20ደቂቃ መሆኑ ነው

ዳዊት፡ አይገርምህም? አስተውየው አላውቅም፤ በነገራችን ላይ ይሄ ሰዓት ከጓደኞቼ ጋር ተገናኝተን ካፌ ውስጥ ሻይ ቡና የምንልበት ሳይጨምር ነው።

መዛኝ፡ ከፈጣሪ ጋር ተገናኝተህ ታውቃለህ?

ዳዊት፡ አይ የኔ ነገር .. ላካሰ ከእብድም ጋር ነው ሳወራ የቆየሁት፤ ከፈጣሪ ጋር እንዴት ልገናኝ እችላለሁ?

መዛኝ፡ አሁን ሚዛኑ ላይ መውጣት ትችላለህ!

/ዳዊት ሚዛኑ ላይ ሲወጣ ቴቄል የሚል ድምጽ ከጀርባ ይሰማል/

ዳዊት፡ ምን ማለት ነው? ምንድን ነው?

መዛኝ፡ በሚዛን ተመዝነህ ፣ ቀልለህም ተገኘህ ማለት ነው።

ዳዊት፡ ቀለድክብኝ ማለት ነው? ሲያስጠላ /በብስጭት የሄዳል/

መዛኝ፡ አንድ ሰው እንዴት ዳዊትም ጎልያድም ሊሆን ይችላል? ለነገሩ ምን ይገርማል? በስም ክርስቲያን በምግባር አህዛባዊ የሆነ ሞልቶ የለም እንዴ ብዙዎቻችን ክርስትና እና ዘመናዊነት ተቀላቅሎብናል።ክርስትናን የሚያስተው ዘመናዊነት፣ ማንነትን የሚያስረሳ ስልጣኔ ገብተል። የሄ ሰው ስጋውን ለመመገብ በቀን 80 ደቂቃ እያጠፋ ነፍሱን ለመመገብ 8ደቂቃ እንዴት ያጣል?

........ተመዘኑ፣ ተመዘኑ .. በምስጢራዊው ሚዛን ተመዘኑ .

ዮሴፍ፡ ስንት ነው?

መዛኝ፡ በነጻ ነው

ዮሴፍ፡ ሚዛኑ በ UNICEF›› ይረዳል እንዴ /ብሎ ሚዛን ላይ ሊውጣ ሲል/

መዛኝ፡ ቆይ ከዚያ በፊት የምጠይቅህ ጥያቄዎች አሉኝ

ዮሴፍ፡ እሺ ቀጥል!

መዛኝ፡ ስምህ ማነው?

ዮሴፍ፡ አባቴ ዮሴፍ እናቴ ደግሞ ትዕግስቱ ይሉኛል፡፡ ደስ ባለህ ጥራኝ

መዛኝ፡ በቀን ስንት ግዜ ትመገባለህ?

ዮሴፍ፡ ምን አገባህ? ደግሞ ሚዛን ምናምን እያልክ ትለፈልፋለህ እንዴ? ስራ ፈት /ብሎ ይሄዳል/

መዛኝ፡ የባሰ አታምጣ! በዚህ ጥያቄ ከተበሳጨ ምኑን ትዕግስቱ ሆነው መታገስ እያቃተን ነገሮች ጀምረን እንዳቁዋረጥን እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው፡፡ ቅዳሴውን አቁዋርጠን ፣ ጉባኤውን አቁዋርጠን ትንሽ ብንታገስ ፍፃሜውን እናየው ነበር፡፡ የመጽሐፍ ቅዱሱ ዮሴፍ የኃጢአት ግብዣን ንቆ ሸሽቶ ሄደ፡፡ ይሄ ደግሞ የጽድቅ ጥሪ ንቆ ተበሳጭቶ ሄደ፡፡ ዱባና ቅል አበቃቀላቸው ለየቅል አሉ እኔኮ የሚገርመኝ ስማችን የማይከብደን ለምን ይሆን?

ተመዘኑ .. ተመዘኑ በምስጢራዊው ሚዛን ተመዘኑ . ተመዘኑ በምስጢራዊው ሚዛን ራሳችሁን መርምሩ፣ በሚዛን መመዘን በምስጢር መመረመር ብልህነት ነው

/3 ጓደኞች እያወሩ ሳያስተውሉት እያወሩ ያልፋሉ/

መዛኝ፡ ነብዩ ኢሳይያስ መስማት ትሰማላችሁ፣ ነገር ግን አታስተውሉም ማየትንም ታያላችሁ ግን አትመለከቱም ያለው እኮ እንደዚህ አይነቶቹን ነው፡፡ ስንት ነገሮችን ጆሮ ዳባ ልበስ ብለን አለፍናቸው! እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መንገድ ሲጠራን እኛ አናስተውልም እኛን አይመለከተንም እያልን እንተወዋለን፡፡ የበረቱት ወዳጆቻችን ዛሬ ጉባኤ አለ፣መዝሙር ጥናት አለ፣የኮርስ ት/ት አለ፣የበረከት ሥራ አለ ተሳተፉ ሲሉን ለማያውቁን ከእግዚር ቤት ላራቁን መቀመጫችን እስኪደነዝዝ ለምናያቸው ፊልሞች የምንሰጠውን አይንና ጆሮ የነፈግናቸው ስንቶቻችን ነን?

ተመዘኑ ተመዘኑ

ሊዲያ፡ እናንተ ባለሚዛኖች የነፍስንም ክብደት የሚያሳውቅ ሚዛን ብታመጡ ጥሩ ነበር

መዛኝ፡ የነፍስ ሚዛን አለኝ ተመዘኚ እህቴ!

ሊዲያ፡ እየቀለድክ ነው? እንዴት አልተወራም?

መዛኝ፡ የሚሰማ ጠፍቶ እንጂ ሁሌ ይነገራል፤ለማንኛውም በቅድሚያ የምንጠይቅሽን ጥያቄዎች ከመለሽ በኃላ በሚዛኑ ትመዘኛለሽ

ሊዲያ፡ እሺ ይሁን!

መዛኝ፡ ስምሽ ማነው?

ሊዲያ፡ የዓለም ስሜ ሊዲያ ነው የክርስትና ስሜ ወለተ ጻድቅ

መዛኝ፡ ከፈጣሪሽ ጋር ተገናኝተሽ ታውቂያለሽ?

ሊዲያ፡ ፈጣሪዬ ከኔ ተለይቶኝ አያውቅም፤ በመግቦቱ በቸርነቱ ሁልግዜ ከኔ ጋር ነው፡፡

መዛኝ፡ አንቺስ ሁልግዜ ከርሱ ጋር ትሆኛለሽ?

ሊዲያ፡ እኔማ ሁልግዜ እክደዋለሁ፡፡ በሆነ ባልሆነው ምክንያት ከቤተክርስቲያን እቀራለሁ፡፡ በጣም የሚገርምህ አንድ ግዜ ጉባኤ ስንማር ወንበር ስላልነበር ድንጋይ ላይ መቀመጥ ስለቻተኝ ትቼው ነበር፡፡ አምላኬን ሁልግዜ የምለምነው በማይመች ጊዜና ሁኔታ እንኳን ቢሆን ከቤቱ እንዳልጠፋ ነው፡፡ ልብሴ ከዶድራንት ይልቅ ዕጣን ዕጣን ሲሸት ደስ ይለኛል፡፡ ዕጣን ሽታው ሰይጣንን ያርቃል፤ ዶድራንት ግን ምናልባት ሰይጣንን

ሳያቀርብ ይቀራል ብለህ ነው?

መዛኝ፡ አሁን ሚዛኑ ላይ መውጣት ትችያለሽ

ሊዲያ፡ እሺ /ብላ ሚዛኑ ላይ ስትወጣ ከመድረክ ጀርባ እንዲህ የሚል ድምጽ ይወጣል/

‹‹ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግስቱንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕመም ሁሉ እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር። ብዙ ሕዝብም ባየ ግዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው በዚያን ግዜ ደቀመዛሙርቱን መከሩስ ብዙ ነው ሰራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው። ማቴ 9፥32

ሊዲያ፡ ምንድን ነው ነገሩ?

መዛኝ፡ የሚዛኑ መልዕክት ነው። ሌሎችንም ማስተማር እንዳለብሽ ምኩራብ በተባለች በቤ/ክ እየተገኘሽ ማገልገል እንዳለብሽ ለተጨነቁት ማዘንና መራራት እንዳለብሽ ሚዛኑ ያስረዳል። በተጨማሪም ገና ብዙ ስራ አለ። ሠራተኞቹ ግን ጥቂቶች ስለሆኑ ያንቺ ድርሻ ተቀምጦ ይጠብቅሻል። በስራሽ ሁሉ እንዲረዳሽ ፈጣሪሽን በጸሎት መጠየቅ እንዳለብሽ ፈጣሪሽን በጸሎት መጠየቅ እንዳለብሽ የሚዛን ውጤትሽ ያሳያል።

ሊዲያ፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ የኔ ወንድም ስንት ነው ክፍያው?

መዛኝ፡ በነፃ ነው

ሊዲያ፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

መዛኝ፡ አሜን ሁልግዜ ተመዘኑ..ሕይወታችሁን በሥጋዊ ጥበብ አዘምኑ!

....ተመዘኑ .ተመዘኑ .በመንፈሳዊ ሚዛን ተመዘኑ

ውጤታችሁ ቴቄል ከሆነ
ከጽድቃችሁ ኃጢአታችሁ ከገነነ
ነፍሳችሁ ከስታለች
በጎ ምግባር ተርባለች
የጽድቅ ሥራ ናፍቃለች
እናም ወንድሜ እናም እህቴ
የሚዛን ውጤትህ "ቴቄል" ደሞዙ መጨረሻው
ትሉ ማያንቀላፋ እሳቱ ማይጠፋ ያው ሲኦል ነው
ታዲያ ከዚህ የከፋ ምን ቅጣት አለ?
ታዲያ ከዚህ የበለጠ ምን አበሳ አለ?
በል ተነስ ያለፈው ዘመን ይበቃሃል
ቸልተኝነት ስንፍናህ ክህደት ጥርጣሬህ በዝቷል
የዘመኑ ፍጻሜም ቀርቧል
እንደጠዋት ጤዛ የሆነ እድሜህን ሳትነጠቅ
የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወም ዘንድ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ታጠቅ
ምሕረት፥ ርኅራኄ፥ ቸርነት፥ ትህትና፥ የዋሀት፥ ትዕግሥትም ልበስ
ታገለግለውና ታመሰግነው ዘንድ በአምሳሉ የፈጠረህ እንድሰኝ ደስ
ከኃጢአት ርቀህ በጽድቅ ተመላለስ )2x

ምንጭ-ከወ/ነጎድጓድ ቅ/ዮሐንስ ቤ/ክ ሰ/ት/ቤት

# ተፈፀመ